# ብፁዕ አቡነ ተስፋሥላሴ መድኅን ካቶሊካዊ ጳጳስ ዘመንበረ ዓዲግራት እና የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የሚሌኒየም በዓል አከባበር አስተባባሪ ኮሚሽን ሰብሳቢ በአዲስ አበባ ልደተ ማርያም ካቴድራል ያቀረቡት አስተንትኖ።

**የኢትዮጵያ ሚሌኒየም**
**የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን**
**የ2000 ዓ.ም. ኢዮቤልዩ፣ የቅዱስ ቁርባን ጉባኤ**
**አዲስ አበባ፣ ልደተ-ማርያም የካቶሊክ ካቴድራል**
**ሚያዝያ 24-26/2000 ዓ.ም.**

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።**

## «ቅዱስ ቊርባን»
## የምሕረት - የዕርቅ - የሰላም - የአንድነት ምሥጢር

«ከሰማይ የወረደ ሕያወ እንጀራ እኔ ነኝ፣ ማንም ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘለዓለም ይኖራል፤ ይህም እንጀራ ለዓለም ሕይወት እንዲሆን የምሰጠው ሥጋዬ ነው። . . . ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው። . . . ሥጋዬ እውነተኛ ምግብ፣ ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና፤ ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል» ዮሐ. 6:51፣ 54-56

መግቢያ

«አሁን እዚህ የምንቆርሰው ያለን ዳቦ፣ ገና ሳይፈጭ በጥሬው ሳለ ተበታትኖ ነበረ። ኋላ ግን ከያለበት ተለቅሞና ተሰብስቦ አንድ ዳቦ ሆነ። እንደዚሁም ደግሞ አባት ሆይ በተለያየ ቦታ ተበታትና ለምትገኘው ቤተክርስቲያን ከሁሉም የዓለም መአዘኖች በአንድ ቦታ ሰበሰባት። ከብዙ የእህል ፍሬ አንድ ዳቦ እንደሚጋገር፣ ከብዙ የወይን ፍሬ ደግሞ ወይን እንደሚጠመቅ፣ እንደዚሁም ደግሞ ምእመናኖችህ አንድ ነፍስና አንድ ልብ እንደሚሆኑ አድርግ» (ዲዲስቂልያ/ ትምሕርተ ሐዋርያት)

የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ኢዮቤልዩን በታላቅ ደስታና መንፈሳዊነት ለማክበር የራሷ አርማና መሪ ቃል ያዘጋጀች ሲሆን በአርማው ላይ ከሚገኙት ስእሎች ዋነኛው የላሊበላ የቅዱስ ቊርባን መስቀል ነው። መስቀል የሰው ልጆች የደህንነት ምልክት ሲሆን መድኃኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ ቁርባን አማካይነት እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከኛ ጋር መሆኑን የሚያሳይ ነው።

የኢዮቤልዩ መርሃ ግብር መጽሔት ካካተታቸው አጀንዳዎች መካከል ደግሞ ዋነኛው ይህ በአገር አቀፍ ደረጃ አሁን እየተካሄደ ያለው የአራት ቀናት የቅዱስ ቊርባን አከባበር መንፈሳዊ ጉባኤ

(Eucharistic Cogress) ነው። ቅዱስ አጐስጢኖስ «የጥልቅ ፍቅር ምሥጢር ሆይ! የአንድነት ምልክት ሆይ! የፍቅር ትስስር ሆይ!» እያለ እንደሚገልጸው (የካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ትምህርተ ክርስቶስ ቁ. 1398)፡ ቅዱስ ቊርባን፡-

- ክርስቶስ የገዛ ሕይወቱን አሳልፎ እስከ መስጠት ለሚያፈቅራትና ሙሽራው ለሆነችው ቤተክርስቲያን (ኤፌሶን 5:21-33) የሰጣት የፍቅር፣ የአንድነት ምልክት፣
- የርኅርኄ ትስስር፣ የሞቱና የትንሣኤው መታሰቢያ ምሥጢር ነው (የሁለተኛው የቫቲካን ጉባኤ ሰነድ፡ ቅዱስ ጉባኤ ቁ.47)፣
- የቤተክርስቲያንና የእያንዳንዱ ክርስቲያን ከፍተኛው የሕይወት ምንጭና መደምደሚያ (የሕዝብ ብርሃን 11፣ ክህነታዊ አስተዳደግ፡ ቁ.5)፣
- የመለኮታዊ ሕይወት ሱታፌ፣ በመንፈስ ቅዱስ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ አምልኮ ማጠቃለያ የሆነ ምሥጢር ነው (የካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ትምህርተ ክርስቶስ ቁ. 1324-25)።

የዚህ ምሥጢር የማያልቅ ሃብት በተለያዩ ስሞች የሚገለጽ ሲሆን፡ ጠቅለል ባለ መልኩ ምሥጢረ ቅዱስ ቊርባን፡

- ለአብ የሚቀርብ ***የምሥጋና መሥዋዕት***፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና በክርስቶስ ቃላት፡ ኅብስትና ወይን መልክ ***ምሥጢርና እውን የሆነ የክርስቶስ ህላዌ*** (የካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ትምህርተ ክርስቶስ ቁ. 1357)፣
- «ይህንን ለኔ መታሰበያ አድርጉት» ሉቃ. 22:19 ባለው መሠረት የሚቀርብ፡ ***የክርስቶስ መሥዋዕታዊ መታሰቢያ***፣
- በቀራንዮ መስቀል እኛን ለማዳን ሕይወቱን ባሳለፈበት ዋዜማ ከአርድእቱ ጋር ባዘጋጀው ***የመጨረሻ እራት*** በክርስቶስ የተሰራ፣
- በቅዳሴ «***አሜን አሜን፣ አምናለሁ እታመንምአለሁ፤ ይህ የክርስቶስ ሥጋውና ደሙ መሆኑን አምናለሁ***» ብለን እንደምንታመነው፡ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሰዋውን የገዛ ሥጋውንና ለብዙኃን ሥርየት ያፈሰሰውን የገዛ ደሙን የሚሰጥበት (የካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ትምህርተ ክርስቶስ ቁ. 1365)፣
- ከምሥጢራት ሁሉ የላቀ በመሆኑ ከሁሉ የላቀ አምልኮአዊ ክብርና ስግደት የሚገባው፣ የላቀ ፍቅር፣ የላቀ ጸጋ የሚሰጥ፣ ***ከሁሉ የላቀ የምሕረት፣ የዕርቅ፣ የሰላም፣ የአንድነት ምንጭና መግለጫ የሆነ ምሥጢር*** ነው።

### ምሥጢረ ቅዱስ ቊርባን የምሕረት፣ የዕርቅ፣ የሰላም፣ የአንድነት ምሥጢር ነው። . . . እንዴት?

እግዚአብሔር አምላካችን ከብርና ከወርቅ እጅግ የከበረ በልጁ ደም የታረቀን (1ጴጥ. 1:18-19፣ 1 ቆሮ. 6:20) ነውርና ነቀፋ የሌለን ቅዱሳን አድርጎ በፊቱ ሊያቀርበን ስለፈለገ ብቻ ነው (ቆሎሴ 1:21-22)። እርሱ ቅዱስ እንደሆነ ቅዱሳን እንድንሆን (1 ጴጥ. 1:15-16)፣ እርሱ ፍጹም እንደሆነ እኛም ፍጹማን እንድንሆን ስለሚሻ ነው (ማቴ. 5:48)።

ወደ ቅድስናና ፍጽምና የሚደረሰው፡ መጀመሪያ ክርስቶስ፡ ራሱ ባስተማረን ጸሎት እንዳስመረበትና (ማቴ. 6:9-13) ለስብከት ወንጌሉ በሰጠን የዕርቅ መልዕክት መሠረት (2 ቆሮ. 5:18-19) ልክ እርሱ ይቅር እንዳለልን እርስ በርሳችን ከልብ ይቅር ተባብለን ስንታረቅ ነው (ኤፌ. 4:32)፣ ቀጥለን ደግሞ ከአምላክ እንድንታረቅ በተጠራነው መሠረት (2 ቆሮ. 5:20) በንስሐ ከአምላካችን ጋር ስንታረቅና በዕርቅ ምሥጢርና መሐድ በሆነው በቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ በሚገባ ተዘጋጅተን (1 ቆሮ. 11:28-29) በትልቅ መንፈሳዊነትና ትህትና አዘውትረን ስንሳተፍ

ነው። ጥላቻና ክፋት በበዛበት ዓለማችን ከቤታችንና ከጕረቤታችን ጀምረን በየአካባቢያችን ባገርም ይሁን በዓለም አቀፍም ሁኔታዎች የዕርቅና የሰላም መሣሪያዎች ለመሆን የተቻለንን ሁሉ ማድረግና ማበርከት ይገባናል።

በተጣሉና በተራራቁ ወገኖች ዕርቅና ሰላም የሚመጣው ለተደረገው በደል ሙሉ ምሕረት ሲሰጥ ነው። ቅ. ጳውሎስ እንደገለፀው በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ እንደ ጸጋው ባለ ጠግነት መጠን በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን፣ እርሱም የበደላችን ሥርየት ነው (ኤፌ. 1:7)። የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ አነጻን/ያነጻናል (1ዮሐ. 1:7)። እንደ ሕጉም መሠረት ከጥቂት በቀር ነገር ሁሉ በደም ነበር የሚነጻ፣ ደምም ሳይፈስ ስርየት አልነበረም (ዕብ. 9:22)። በቀራንዮ ኮረብታ መስቀል ላይ በፈሰሰ ደሙ ክርስቶስ ከበደላችን አንጽቶ የኃጢአታችን ሙሉ ሥርየት ማለት ምሕረትን አገኘልን። የዘለዓለም ኪዳን በሆነው (ዕብ. 13:20) ክቡር ደሙ (1ጴጥ. 1:18-19) ምክንያት ደግሞ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የመግባት ዕድል አገኘን (ዕብ. 10:19)። ምስጢረ ቅዱስ ቊርባን ደግሞ እኛ ለክፋታችን ምሕረትና ሥርየት እንድናገኝ ክርስቶስ «የመዓዛ ሽታ የሚሆን መባእንና መሥዋዕትን አድርጎ ስለኛ ራሱን አሳልፎ የሰጠበት» መሥዋዕት መታሰበያ ምሥጢር ነው፤ በዚህም ምክንያት ቅዱስ ቊርባን የሕምረት ምሥጢር ነው።

በሕይወት - ኑሮአችን?

እግዚአብሔር አምላካችን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሳ (ኤፌ. 2:4) በርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲያገኝ አንድ ልጁን እስከ መስጠት ዓለምን ወደደ (ዮሐ. 3:16)። ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ይሰጥ ዘንድ የመጣው አንድ ልጁ ደግሞ (ማር. 10:45) በኃጢአት ምክንያት በሰውና በፈጣሪው መካከል የነበረውን የጥል ግድግዳን በሥጋው በማፍረስ ሰውን ከአባቱ ጋራ አስታርቆ ሰላምን አመጣ (ኤፌ. 2:16)። ይህ ሊሆን የቻለው ግን የሚገባን ሆኖ ወይም እኛ ተባብረነው ሳይሆን እግዚአብሔር አምላካችን እኛ ገና ደካሞች ሳለን፣ ገና ጠላቶቹ ሳለን በፍቅሩ ብዛት በደላችንን ሁሉ በመደምሰስ (2 ቆሮ. 5:19) በቀራንዮ መስቀል ላይ በፈሰሰ በክርስቶስ ባንድ ልጁ ደምና ሞት በመካከላችን ሰላም እንዲኖር አድርጎ በሰማይም በምድርም ላለነው ከራሱ ጋር (ቆሎሴ 1:20) ስላስተረቀን ብቻ ነው (ሮሜ. 5:6.8.10)። ቅዱስ ቊርባን ደግሞ ይህ ክርስቶስ በቀራንዮ መስቀል ላይ ተሰቅሎ ሕይወቱን ለኛ ሲል በማሳለፍ በፈጣሪና በሰው ልጅ መካከል የዕርቅ ሥርዓት ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመፈጸም የአዲስ ኪዳን ደሙን ያፈሰሰበት መሥዋዕት (ሉቃ. 22:20)፣ የክርስቶስ የሞቱና የትንሣኤው መታሰቢያ ምስጢር ነው። በዚህም ምክንያት **ቅዱስ ቊርባን እጅግ ትልቅ የዕርቅና በሱ በሚመጣው የሰላም ምስጢር** ነው።

ክርስቶስ መስቀል ላይ ተንጠልጥሎ ሳለ እስትንፋሱ ከማለፏ በፊት ያደረገው የትልቅ ፍቅሩ መግለጫ የሆነው የመጨረሻ የማዳን ሥራ «አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው» (ሉቃ. 23:34) በማለት ለገዳዮቹ ምሕረት መስጠትና መለመን ነበረ። የቅዱስ ቊርባን ምሥጢር ሲሰራ ማታ ያርድእቱን እግር አጥቦ እንደጨረሰ «እኔ እንዳደረግሁላችሁ እናንተም እንደዚሁ እንድታደርጉ ምሳሌ ትቼላኋለሁ» (ዮሐ. 13:15) ባለው መሠረት ደግሞ የእግዚአብሔር ምሕረትና ፍቅር የቀመሰ አማኝ ሁሉ ቂምና በቀል ከከልቡ አስወግዶ «እርስ በርሳችሁም ቸሮችና ርኅሩሆች ሁኑ፤ እግዚአብሔር ደግሞ በርክስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ» (ኤፌ. 4:32፣ ቆላሲ. 3:13) በተባለው መሠረተ ለበዳዩ ምሕረት በማድረግ ደቀ መዝሙርነቱን በሕይወቱ መመስከር አለበት። ይህ ደግሞ ከቤትና ከጕረቤት መጀመር ያለበት መንፈሳዊ ክርስትያናዊ የፍቅር ሥራ ነው። በሱ በቅዱስ ቊርባን ማዕድ በሚሳተፉ መሀከል የይቅርታ ሰጪነትና

የይቅርታ ተቀባይነት በረከት አይለያቸውም፡፡ ይህንን በረከት ደግሞ በዕለት ኑሮአቸው ወደ ቤተሰብ፣ ወደ ጓደኛ ቤት፣ ወደ ሥራ ቦታ፣ ወደ ጐረቤት ይዞ መጓዙና ማሰራጨቱ አይቀርም፡፡ ይህ የክርስቲያን ሐዋርያዊነት ተልእኮ ምሥጢር ነው፡፡

የሁለተኛው የቫቲካን ጉባኤ አባቶች «ቅዱስ ቍርባን የተሰራበት ምክንያት የፍቅርና ያንድነት ምልክት ሆኖ ለነፍሳችን የመንግሥተ ሰማያት መያዣና የጸጋ ሰጪ እንዲሆንለት ነው» (ሥርዓት አምልኮ ቁ.47) እንዳሉት ቅዱስ ቍርባን የፍቅርና ያንድነት ምሥጢር ደግሞ ነው፡፡ ይህ አንድነት መሠረቱ በቅድስት ሥላሴ አካላት በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለ ዘለዓለማዊ አንድነት ነው፡፡ የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች አንድነት በጸሎት ያላቸውን በጋራ በመካፈልና በትምህርተ ሐዋርያት ላይ ብቻ ሳይሆን በዋናነት በቅዱስ ቍርባን መአድ ሱታፌ ላይ የተመሠረተ ነው የነበረው (የሐዋ. ሥራ 4:32-35)፡፡ አንድ ጌታ፣ አንድ እምነት፣ አንዲት ጥምቀት፣ አንድ አምላክና አባት ያላቸው (ኤፌ. 4:5)፣ ሰውነቱ የሆነችው ያንዲት ቤተክርስቲያን አካሎች (ሮሜ 12:5) የሆኑት ክርስቲያኖች ብዙዎች እንኳ ቢሆኑም ከክርስቶስ ደም ጋራ አንድነት ባላት ካንዲት ጽዋ ስለሚጠጡ፣ እንዲሁም ደግሞ ከክርስቶስ ሥጋ ጋራ አንድነት ካላት ከአንዲት ኅብስት ስለሚበሉ (1ቆሮ. 10:16-17) ከሚቀበሉት ክርስቶስና እርስ በርሳቸው መካከል የጸና አንድነት ይመሰርታሉ፡፡ በዚህም ምክንያት **ቅዱስ ቍርባን የአንድነት ምሥጢር** ነው፡፡

ክርስቶስ ከዚህ ዓለም ተልእኮውን ጨርሶ ወዳባቱ ከመመለሱ በፊት ወደርሱ ባደረገው ክህነታዊ ጸሎት በስሙ በሚያምኑና በሚጠሩ ወገኖች መካከል እንዲኖር የተመኘው አንድነትም ሆነ (ዮሐ. 17:20-26) ቅዱስ ጳውሎስም የሚመኘው የነበረ ተመሳሳይ የቃል፣ የልብና የሐሳብ አንድነት (ፊሊ. 1:10) ምንጩና መሠረቱ የቅዱስ ቍርባን ምሥጢርና ሱታፌ ነው፡፡ በቅዱስ ቍርባን ምሥጢር በመሳተፍ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከምንቀበለው ክርስቶስ ጋር የምንመሠርተው አንድነት በሰላም ማሰርያ አስረን ልንጠብቀው ደግሞ ይገባል (ኤፌ. 3:4)፡፡

ፍቅራችንና አንድነታችንን በተመሳሳይ እምነት ባለን ወገኖች መካከል የሚወሰን ብቻ ሳይሆን ከተቀሩት ክርስቲያን ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን ጋርም ልንጋራውና ልንገልፀው ይገባል፡፡ ክርስቶስ ስላልተከፋፈለ (1ቆሮ. 1:13) ወዳባቱ ሲጸልይ እንደተመኘው እርሱና አባቱ አንድ እንደሆኑ ሁሉ (ዮሐ. 17:11) እኛም እንደ መሪዎች ሆነ እንደ ምዕመናን የመከፋፈልን ኃጢአትና ዕንቅፋት አስወግደን በስሙ የምናምንና የምንጠራ ክርስቲያን ወገኖች ሁላችን አንድ እረኛና አንድ መንጋ ወደምንሆንበት አቅጣጫ አልመን በጽናትና ቁርጠኝነት የመሥራትና የመጸለይ መንፈሳዊ ግዴታ አለብን፡፡

የቅዱስ ቍርባንን ምሥጢር አዘውትረን በመሳተፍ የጌታ ምሕረቱንና ዕርቁን ሰላሙንና አንድነቱን ከርሱም ሆነ እርስበርሳችን መካከል ማግኘት ማበልጸግና ስንችልና ሲገባን በግልም ሆነ እንደ ቤተሰብ ወጣት እንሁን አዎቂዎች ቤተክርስቲያን መጥተን በኅብረት ቅዳሴ አስቀድሰን በሥጋ ወደሙ ማዕድ መሳተፍ የማያስችለን ምን አጥጋቢ ምክንያት ቢኖር ነው ተሳትፎአችን እየቀነሰና እየተዳከመ የሚታየው? አንዳንድ ምዕመናን (ወጣቶችም ሆኑ አዋቂዎች) ከሚያቀርቧቸው ምክንያቶች መካከል «ቅዳሴ ረዘመ፣ በማንሰማው ቋንቋ ሆነ፣ ሰዓቱ የማይመች ሆነ፣ ስብከት የዕለቱ ንባባት መልእክትንና የኛን ሕይወት የማያገናዝብ ሆነ፣ ጊዜው ከትምህርት ወይም ከሥራ ስዓት አልጣጣም አለ፣ ሥርዓተ አምልኮው ቀዝቃዛ (ደባሪ) ሆነ»፡ የሚሉ ይገኙ ባቸዋል፡፡ ግን እነዚህ በእውነት በቂ ምክንያቶች ናቸው ወይ?

ከሁሉ አስቀድሞ መታወቅ ያለበት ነገር የሁሉም ምሥጢራት ቅዱሳን ነገሮችና ማኅሌት በጠቅላላ የአምልኮ መጀመሪያና መደምደሚያው ምሥጢር ቅዱስ ቍርባን የሚሰራበት

መሥዋዕተ ቅዳሴ ነው:: ክርስቶስ በራሱ መሥዋዕት ነው ዓለምን የማዳን ሥራ የፈጸመውና የደመደመው:: **የማዳን ሥራው አሁንም ቢሆን አየቀጠለ ያለው በመሥዋዕተ ቅዳሴ ነው::** በዚህም መሠረት ቤተክርስቱያን ከመጀመሪያው አንስታ «ይህንን ለእኔ መታሰቢያ አድርገት» ሉቃ. 22:19 ለሚለው የጌታ ትዕዛዝ ታማኝ ሆና ቆይታለች (የሐዋ. ሥራ 2:42-46):: የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች በክርስቶስ የትንሣኤ ዕለት በሆነው የሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን (እሁድ) ብቻ ሳይሆን (የሐዋ. ሥራ 20:7.11፣ 1ቆሮ. 16:2) እንዲሁም በየቀኑ (የሐዋ. ሥራ 2:46-47) «እንጀራ ለመቁረስ» (የሐዋ. ሥራ 2:42.46) ይሰበሰቡ ነበር:: ከዚያ ዘመን አንስቶ እስካለንበት ጊዜ ድረስ የቅዱስ ቊርባን ሥርዓት ያንኑ መሠረታዊ መልኩን ጠብቆ መቀጠሉ ቅዱስ ቊርባን ዛሬም የቤተክርስቲያን ሕይወት/ልብ ማዕከል ሆኖ እንደሚገኝ (የካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ትምህርተ ክርስቶስ ቁ. 1342-43) ሆኖም እንደሚቀጥል ያስረዳል (ቁ. 1344):: ዘመነ ተሃድሶ የወለዳቸውና ገና በመወለድ ላይ የሚገኙ የክርስትና ሃይማኖት ማሕበረሰቦች በተለይም ምሥጢረ ክህነት ስለሌላቸው ይህንን የቤተክርስቲያን ሕይወት መሠረትና ምንጭ የሆነውን የቅዱስ ቊርባንን ትክክለኛ እሱነቱ በምላት አልጠበቁም፤ አይጠብቁምም:: በዚህም ምክንያት ነው ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ከነዚህ ቤተክርስቲያናዊ ማሕበራት ጋር መሥዋዕታዊ ተሳትፎ ሊኖራት የማይችለው (የካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ትምህርተ ክርስቶስ ቁ. 1400):: የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ግን ከሐዋርያት የወረሱዋቸው ምሥጢረ ክህነትና ቅዱስ ቊርባን፣ እንዲሁም ደግሞ ሌሎች ምሥጢራት ስላሉዋቸውና ለቅዱስ ቀርባን ታላቅ ክብርና ፍቅር ስለሚገልጹ ከነርሱ ጋር አሁንም እጅግ የቀረበ ልባዊ ግንኙነት አለን፤ ወደሚፈለገው አንድነትና ሙሉ ሱታፌም ተግተን አብረን እየሰራንና እየጸለይን ነው (የካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ትምህርተ ክርስቶስ ቁ. 1399)::

ቅዱስ አባታችን ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዮሐንስ ጳውሎስ ዳግማዊ፤ ፀሎተ ሐሙስን ምክንያት በማድረግ በሆስፒታል ካሉበት ለካህናት በጻፉት የመጨረሻ መልእክታቸው «. . . **መላዋ ቤተክርስቲያን ሕይወት የምታገኘው ከቅዱስ ቊርባን ነው»** ብለዋል (ቁ. 1፣ መጋቢት 18/2005 እ.ኤ.አ. «ይህንን ለኔ መታሰበያ አድርጉት» ቁ.33):: ቅዱስ ቊርባን የሚሰራበት መሥዋዕተ ቅዳሴ እንግዲህ ከክርስቶስ ስለ ወረደ የሥርዓተ አምልኮ፣ የቤተክርስቲያን ሕይወት ምንጭና ቁንጮ ነው (ይህንን ለኔ መታሰበያ አድርጉት ቁ.36)::

ከቅዳሴ ምሬት የሚደረግ ማኅሌትና የተለያዩ ጸሎቶች ቅዳሴን የሚተኩ ሳይሆኑ ለቅዳሴ የሚያዘጋጁ ናቸው:: ከቅዳሴ በኋላ የሚደረጉ ደግሞ በቅዳሴ ለቀረበው መሥዋዕት ለአምላክ ምሥጋና ለማቅረብ የሚደርሱ ብቻ ናቸው:: **ስለዚህ ቅዳሴ ከሁሉ የላቀና አማኝ ሁሉ በታላቅ መንፈሳዊነትና ንቃት አዘውትሮ ሊሳተፍበት የሚገባ የአምልኮ ሥርዓት ነው::**

የመሥዋዕተ ቅዳሴ የአምልኮ ሥርዓት በርግጥ ከጥንታዊ መሠረቱ የተዘናበለ እንደሆነ ለመመለስ፣ በቅዳሴ ጊዜ ተሳታፊ እንጂ ታዛቢ ስላልሆኑ (ቅዱስ ጉባኤ ቁ. 30፣ 48) ባግባቡና በቋንቋው ሕዝበ ክርስቲያንን በንቃት ሙሉ በሙሉ እንደሚያሳትፍና ልባቸውን እንደሚነካ ለማድረግም ሆነ በሚመቻቸው ስዓትና ቦታ ለማቅረብ ኃላፊነቱ ዕውቀቱና ችሎታው ባላቸው ሰዎች አስፈላጊ ማሻሻያዎች ሊደረጉ ይገባል (ቅዱስ ጉባኤ ላ. 40፣ 44፣ 45፣ 50):: በሰበካዎች እንዲሁም ደግሞ በሀገር ደረጃ በካቶሊካውያን ጳጳሳት ጉባኤ በተወከሉ ጳጳስ የሚመራ የሊጡርጊያ ኮሚቴ ተቋቁሞ በትጋትና በጥልቀት እያጠና እየሰራበት ያለ ጉዳይ ነው::

- የአምልኮው ሥርዓት በርግጥ ተሳታፊዎቹ በሙሉ የሚረዱትና በንቃት የሚሳፉበት፣
- ስብከትም በዕለቱ ንባባትና ሊጡርጊያዊ ዘመን እንዲሁም ደግሞ ከምእመናን ወቅታዊ ሁኔታ ጋር በቀጥታ የተዛመደ፣

- የቅዳሴ ሰዓትና ቦታ ደግሞ በተቻለ መጠን ለሁሉም ባይቻል ላብዛኛው የሚመች መሆን ይኖርበታል::
- የሚዘመሩ መንፈሳዊ መዝሙሮችም ከቅዱሳት መጻሕፍት የተዋጡና የቤተ ክርስቲያናችንን እምነትና ትምህርት በትክክል የሚያስተጋቡና የሚያንፀባርቁ የቤተክርስቲያን የድኅነት ምሥጢራትን ፀጋ ትርጉም ከሕይወታችን ነባራዊ ሁነታ የሚቃኙ ባጠቃላይ በጳጳሳትና በሰበካቸው ሐዋርያዊ ሥራ መሪዎች የተጠኑና የተደገፉ መሆን ይገባቸዋል::

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በአንዳንድ የአምልኮ ጉባኤዎችና የክርስቲያን ማሕበራት እንደሚደረገው አምልኮ በመንፈሳዊ ትምህርትና ሁሉም ጉባኤተኛ በጭፈራ መልክ በሚሳተፍበት መዝሙር ብቻ ከተወሰነ፣ በርግጥ ጉደሎ አምልኮ ነው:: <u>ስሜትን እንጂ መንፈሳዊ ሕይወትን የማይመግብ</u>፣ ከስሜትም ጋር አብሮ የሚበርድ፣ እምነትን የማያሳድግና የማያጸና አምልኮ ነው:: ለስሜትና ጊዜያዊ ተሳትፎ እንዲመች ተብሎ አምልኮ ምሥጢሩንና ሥርዓቱን ባልጠበቀና በማይገለጽ መንገድ መደረግ የለበትም:: ለአምልኮና ቅዳሴ ጊዜ የሚቀርቡ መዝሙሮች ይዘትና ቅኝት፣ እንዲሁም ደግሞ የሙኪቃቸው ድምፀ-ባዕም: <u>የጸሎትን መንፈስ የሚያውኩና የሚበትኑ ሳይሆን: እርሱን በሚረዱበት መልክ በጥንቃቄ የተመረጡና ለምእመናን ሁሉ ልመናቸውንና ምስጋናቸውን በጥልቅ መንፈሳዊነትና ትሕትና ወደ እግዚአብሔር ለማሳረግ የሚያስችሉ</u> መሆን አለባቸው::

ምእመናን በንቃትና በብቃት መሳተፍ እንዲችሉ ጸሎቶቹንና ዜማውን ከተቻለ ሊማሩ (ቅዱስ ጉባኤ ቁ.30) ባይሆን በቅዳሴ ወቅት በመከታተል እንዲለምዱ ድሮ የተማሩና የሚችሉ እየመሯቸው ሊያለማምዷቸው ይገባል::

ሥርዓተ አምልኮው «ቀዘቀዘ፣ ደበረ» ወይም «ረዘመ» ተብሎ ግን በቂ ባልሆነ ምክንያት:-

- በተለይ በየእሁዱና በበዓላት ወቅት ለቅዳሴ ሳይመጡ መቅረት፣
- መጥተውም ሳይቆርቡ መቅረት
- በንስሃ በሚገባ ሳይዘጋጁ መቍረብ
- በቅዳሴ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በንቃት አለመሳተፍ
- ለቅዳሴ ዘግይቶ መምጣትም ሆነ አቋርጦ መሄድ

ከግንድ እንደተለየ ቅርንጫፍ በንፋስ ወደ ሞት የሚያመሩ ሁኔታዎች ናቸው (ዮሐ. 6:53፣ 15:6):: ጥንቃቄ ማድረግ ይገባናል:: እያንዳንዱ አማኝ ወደ ጌታ ማዕድ በተህትና፣ በንሰሐ፣ በተሰበረ ልብ በመቅረብ (መዝ. 51፣) (የካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ትምህርተ ክርስቶስ ቁ. 1385-88): መንፈሳዊ ሕይወቱን በአምላክ ቃልና በልጁ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደም መመገብ ይኖርበታል (ማቴ. 4:4፣ ዮሐ. 6:32-65)::

<u>በቅድስት ቤተሰብ አምሳያ</u> (ማርያምና ዮሴፍ ኢየሱስን በመሃከላቸው አድርገው ወደ ቤተመቅደስ እንዳመሩ: ሉቃ.2) ክርስቲያን ቤተሰቦች ደግሞ በቤታቸው ሥጋ መአድ ዙርያ አንድነታቸውንና ፍቅራቸውን እንደሚገልጹ ሁሉ በተመሳሳይና በበለጠ መንገድ (ባል፣ ሚስት፣ ልጆቻቸው) እንደ ቤተሰብ አብረው ቤተክርስቲያን መጥተው፣ አስቀድሰው በክርስቶስ የሥጋውና የደሙ ማዕድ በኅብረት በመሳተፍ መንፈሳዊ አንድነታቸውንና ፍቅራቸውን ማበልጸግ ደግሞ ይጠበቅባቸዋል:: ከምሥጢረ ቅዱስ ቍርባን ሱታፌ በሚገኝ ፀጋ የሚኖር ክርስቲያናዊ ቤተሰብ በትዳር ወስጥ ሊፈጠሩ ከሚችሉ ያለመግባባትና የፍቺ አደጋዎች ድኖ መንፈሳዊ የመቻቻል፣ የዕርቅ፣ የሰላም የአንድነት በረከት የሞላበት ይሆናል፤ አባሎቹም ከቤት ውስንነት ወጥተው በኅብረተሰቡ ውስጥ

የዕርቅ የሰላምና የአንድነት ሐዋርያት በመሆን የዓለም ጨውና ብርሃን የመሆን ተልእኮአቸው በሚገባ ይወጣሉ (ማቴ. 5:13-14)::

<u>ወጣቶች</u> ከመንፈስና ሥጋ ጉጂ የሆነ ስሜት ርቀው (2 ጢሞ.2:22) በቃል፣ በአኗኗር፣ በፍቅር በእምነትና በንጽሕና አብነት ይሆኑ ዘንድ (1 ጤሞ.4:12) ዋሊያ የውኃ ምንጭን እንደምትናፍቅ በመዝሙር ብቻ ሳይሆን በበለጠ በሥጋውና በደሙ ክርስቶስን ለመገናኘት ሊናፍቁና በንቃትና መንፈሳዊነት ሊሳተፉ ይገባል (መዝ. 42-23)::

ቅዱስ ቊርባን የሱታፌ ምንጭና መገለጫ በመሆኑ ቅዱስ ቊርባን መቀበል ማለት ከኢየሱስ ጋር መሠረታዊ ህብረት መፍጠር ነው:: «በእኔ ኑሩ፤ እኔም በእናንተ እኖራለሁ» ዮሐ. 15:4::

ከኤማሁስ አርድእት ታሪክ እንደምንረዳው ክርስቶስ «<u>እነሆ እኔ እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ</u>» ማቴ. 28:20 ብሎ ለደቀመዛሙርቱ የሰጠው ተስፋ በሕይወታችን በጉልህ እውን ሆኖ የሚኖረው በቃሉና ሥጋውና ደሙ በሆነው መሥዋዕተ ቅዳሴ በየዕለቱ በመንበረ ታቦት ላይ «በሚቆረሰው እንጀራ» ስለሆነ (ሉቃ. 24:13-32) አማኞች ሁላችን ይህንን ተገንዝበን የፍቅር፣ የምሕረት፣ የዕርቅና የአንድነት ጸጋን የሚሰጠውን የቅዱስ ቊርባን ምሥጢር ቤተክርስቲያናችን እንደምታስተምረውና እንደምታዘው በእሁድና በበዓላት ከተቻለም በየቀኑ በመቀበል (የካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ትምህርተ ክርስቶስ ቁ. 1389) እንደ የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች (የሐዋ. ሥራ 4:32-35) አንድነታችንን ከእርሱ ከክርስቶስና ከእርስ በርሳችን እናጉልብት፣ እናሳድግ (የሐዋ. ሥራ 2:42፣ 1ቆሮ. 11:10-16)::

የመጀመሪያይቷ ቅዱስ ፃጥን በመለኮታዊ ልጅዋ ከመስቀል ላይ ሆኖ የተሰጠችን ፈራይተ-ቊርባን ርሕርሕትና ቅድስት እናታችን ድንግል ማርያም ከኢየሱስ ጋር ከእኛ ጋር ሆና «ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች፣ መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒነ ሐሴት ታደርጋለች» ሉቃ. 1:47 እንዳለች፤ እኛ ም በጥበቃዋ ሥር ሆነን ሁልጊዜ ዘወትር አብረናት እንዘምር::

**«ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት፣ ዛሬም ለዘለዓለምም ያው ነው::» ዕብ. 13:8**

+አቡነ ተስፋሥላሴ መድኀን
ካቶሊካዊ ጳጳስ ዘመንበረ ዓዲግራት
የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን
የሚሌኒየም በዓል አከባበር አስተባባ ኮሚሽን ሰብሳቢ

= = = = =

ኢየሱስ «ይህንን ስታደርጉ የኔን መታሰቢያ አድርጉ» ሲለን በመለኮታዊ ሕይወቴና ፍቅሬ እንድሞላችሁ ዘንድ ራሳችሁን ስጦታ እንድታቀርቡልኝ ጋብዤያችሁአለሁ እያለን ነው።

ለአስተንትኖ፤

1. ኢየሱስ በቅዱስ ቊርባን ራሱን የሰጠን ለምንድነው?
    - ኢየሱስ ይወደናል፣ ስለሆነም በቀጣይነት ራሱን ሊሰጠን ስለሚፈልግ
    - ቅዱስ ቊርባን የእርሱ በማያቋርጥ መልክ በኛ ውስጥ መኖሩን ማረጋገጫና ማሳሰበያ
    - በጣም ልዩ በሆነ መንገድ ራሱን የሚሰጠን መሆኑ ያሳያል
    - ልዩ የመለኮታዊ ዕርቅ መንገድ
2. ኢየሱስ በቅዱስ ቊርባን ያሳየን መንገድ ከምን ወደምን የሚመራን ነው?